# የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

**Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)**

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com


ጥቅምት 2፣ 2107

## አገርን ከጥፋት ህዝብን ከፍጅት ለማዳን ዛሬውኑ በጋራ እንነሳ

በአገራችን ውሰጥ የሰፈነው ከፋፋይ ሥርዓት እነሆ ህዝባችንን እርስ በርስ የሚያጋጭና የአገሪቱንም አንድነት ከፍተኛ አደጋ ላይ የጣለበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ሕዝባችን በየዕለቱ ከአንድ ቀውስ ወደ ሌላ ቀውስ እየተሸጋገረ ይገኛል። የቀውሱ አድማስም በአንድ ቦታ የተወሰነ ሳይሆን በየጊዜው እየሰፋ ትላንት ሰላም ነው ይባል የነበረን ቦታ ዛሬ የቀውስ ማዕከል እያደረገው ሁሉንም የኅብረተሰባችንን ክፍል፣ ሁሉንም ቋንቋ ተናጋሪ እየነካ ይገኛል። በቀላል አነጋገር አገሪቱ ከዳር እስከ ዳር በቀውስ እየተናጠች መሆኗ በገሃድ እየታየ ነው።

ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ላለፉት 26 ዓመታት ሲካሄድ የቆየውን አመቃ፣ ምዝበራና ንቅዘት በመቃወም የተነሳው ህዝባዊ እንቅስቃሴ በዋናነት የሚጠቀስ ሲሆን፣ ይህን ተቃውሞ ተከትሎ የተከሰተው የሥርዓቱ ውስጣዊ መፈራረስ ያስከተለው መዘዝ መሆኑን መታዘብ ይቻላል። የዚህ ሁሉ ውጤት ደግሞ፣ ሁላችንንም ሊያሳስብ የሚገባ ነገር፣ የሥርዓቱ መፍረስ በህዝባችን ደህንነትና በአገራችን ህልውና ላይ የሚድቅነው አደጋ ነው።

በሀገራችን ውስጥ የሚታዩት ችግሮች ዘርፈ-ብዙና ውስብስ ቢሆኑም በዋናነት ሥርዓቱ ከሚያራምደው ህዝብን እርስ በርስ በጠላትነት እንዲተያይ ከሚያበረታታው፣ የጋራ እሴቶችን ማጉላትና ማጠናከር ሳይሆን ሆን ብሎ በሚያዳክመው፣ ዴሞክራሲያዊነት የሌለው የሀገሪቱን ችግሮች በሸፍጥና በጉልበት ለመፍታት ከሚጥረው አምባገነን አሸባሪ ሥርዓት ፖሊሲና ተግባር ጋር የተዛመደ ነው።

ኢትዮጵያ ዛሬ በአራቱም ማዕዘናት ህዝብ ለዘመናት ከኖረበት ቀየው የሚፈናቀልባት፣ ዜጎች "ይህ ድንበር የኔ ነው ያ ደግሞ ያንተ አይደለም" እየተባሉ እንደውጭ ዜጋ ከሚገለሉበትና ከሚባረሩበት፣ በሀገራቸው ጉዳይ ያላቸውን አመለካከት በነፃነት የማይገልጡበት፣ የሥርዓቱ ባለሥልጣኖችና ታማኞቻቸው ደግሞ በማንኛውም ኢትዮጵያዊና በንብረቱ ላይ እንደፈለጉ የሚያዙበት፣ ህዝብም ከግፉ መብዛት፣ ከዋስትናና ፍትህ ማጣት የተነሳ በራሱ አገር ውስጥ በሞትና በሕይወት መኖር መሀል ያለው ትርጉም የጠፋበት ሁኔታ ላይ ደርሰናል።

በፖለቲካው መድረክ ዛሬ የሚታየው የህወሓት መራሹ የኢህአዴግ ፍጹም አምባገነንነት ነው። የፌደዴል ሥርዓት የሚባለውም ከተጻፈበት ወረቀት በላይ ዋጋ የሌለው የህዝብ መብት የማይከበርበትና ለይስሙላ ብቻ የተቀመጠ በህወሓት መራሹ ኢህአዴግ በፍጹም ማዕከላዊነት የሚሽከረከር ሥርዓት ነው። የሥርዓቱ ብሄር ተኮር የፖለቲካ ቅኝት፣

አደረጃጀትና የክልል አሸናሸን ያሰከተለው ወደ ውስጥ የመመልከት ክስተት ህዝባችን እርስ በርሱ እንዲጠራጠር የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ አንዱ የሌላው ጥቅም እንቅፋት ወይም ታሪካዊ ጠላት ሆኖ እንዲታይ በገገርው ቡድን ሲለፈፍ የቆየው ተንኮል አሁን በአንዳንድ ቦታዎች ውጤቱ መታየት ጀምሯል።

ሸንጎ ከጥቂት ወራት በፊት ባወጣው ሰፊ ጥናታዊ ጽሁፍ እንዳመለከተው "በአሁኑ ሰዓት በአገሪቱ ውስጥ ለምን እጅግ ሰፊ የሆነ የድንበር ግጭት ተከሰተ የሚለውን ለመረዳት ደግሞ በዚህ ሥርዓት መሬት የብሄር/የብሄረሰብ ነው መባሉ ይህም "እኛና እነሱ" የሚለውን ድንበር ይበልጥ እንዲሰፋ እንዳደረገውና የማያባራ ግጭትን ለመቀስቀስ ዋነኛው ምክንያት እነደሆነ ገልጦ ነበር።

በማያያዝም ያስተዳደር ክልሎች በብሄር ተኮር እንዲሸነሸኑ መሆናቸው በህዝባችንና በአገራችን አንድነት ላይ ታላቅ አደጋን አጥልቷል። በዚህ ፖሊሲ ምክንያት እጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያን ተፈናቅለዋል፣ ንብረታቸው ተነጥቋል፣ ሕይወታቸው ጠፍቷል። ይህ ከቀጠለ እጅግ ሰፊ የእርስ በርስ ግጭት የሚጋብዝ እንደሆነ ሸንጎ ይገነዘባል ብሎ ነበር።

ይህ ሁኔታ እነሆ በቀጣይነት ህዝባችንን እያመሰና እጅግ አሰፈሪና አሳዛኝ ወደሆነው የእርስ በርስ ጦርነት የሚገባበትን ሁኔታም እውን እያደረገ ይገኛል። በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለዓመታት በመካሄድ ላይ የሚገኙት ግጭቶች እየባባሱና እየተጠናከሩ እንጂ እየከሰሙ አይደለም። አሁን የደረስንበት ደረጃ በብሄረሰቦች መካከል የተከሰተው ቀውስ ህዝብንና ሥርዓቱን ብቻ ሳይሆን የሥርዓቱን የተለያዩ አካሎችም ወደ ግልጥ በመሣሪያ የታጀበ ግጭት እንዲገቡ አድርጓቸዋል።

ከሁሉም በላይ ያሁኑን በኦሮሞና በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል አካባቢ የተከሰተውን ግጭት እጅግ ለየት የሚያደርገው የተጠቀሰው የእርስ በርስ ግጭት በህዝብ ደረጃ ወይም ከተቃዋሚ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ሳይሆን በራሱ በሥርዓቱ ተባባሪ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ማለትም "የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልላዊ መንግሥት"ና "የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት" የፖሊስ ኃይሎች ሙሉ በሙሉ የተሳተፉበት መሆኑ ነው። ሁለቱም የገኘው ህወሓት መራሹ ኢህአዴግ አባልና ደጋፊ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ መሪዎቻቸውም በሀገሪቱ ደረጃ የተቀመጠው አገዛዝ አካል ጭምር ናቸው። ስለዚህም ራሱ ህወሓት/ኢህአዴግ የግጭቱ ዋና ተዋናኝ ነው ማለት ነው። አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ እንዲሉ፣ ህወሓት መሩ የኢህአዴግ አገዛዝ በራሱ ፖሊሲ ምክንያት በአገዛዙ አባላት እየተካሄደ ባለው ቀውስ ራሱ መፍትሄ ፈላጊ፣ ራሱ ፍትህ አስፋኝና ቀጣይ ሰላም ፈጣሪም ሊሆን አይችልም፡፡

ይህን ማድረግ ችግሩን አደፋፍኖ ለተወሰነ ጊዜ ለማፈን ያስችል ይሆናል እንጂ መፍትሄ አይሆንም። በኢትዮጵያ ሶማሌም ሆነ ኦሮሚያ በሚባለው ክልል እንዲሁም በሌሎች የሀገራችን ክፍሎች ውስጥ የሚታዩትን እጅግ የተወሳሰቡ ችግሮች ለመፍታት ሁሉም ባለድርሻዎች ሊመክሩበትና የመፍትሄው ባለቤት ሊሆኑ ይገባል።

ችግሮቻችን ራሳቸው ከሥርዓቱ ራዕይ፣ ፖሊሲወችና ተግባር መጣመም የሚመነጩ ስለሆነ፤ የሥርዓቱ ቁንጮ የሆነው ህወሓት መራሹ ኢህአዴግም የዚህ ብሄራዊ ምክክር አንዱ አካል ሊሆን ይችላል እንጂ ብቸኛው መፍትሄ ፈላጊ ከቶ ሊሆን አይችልም።

ሥርዓቱ ላለፉት 26 ዓመታት የተቀሰቀሱ ቀውሶችን "በትክክል ተረድቻለሁ ስለሆነም መፍትሄውን ይገባ እቀርባለሁ" በማለት ችግሩን መፍታት ሳይሆን ሥልጣኑን ማጠናከርና ይበልጥ ችግሮችን ለማባባስ የተጓዘበት ጎዳና እንዳልሠራ የሥርዓቱ መሪዎችና ደጋፊዎቻቸው አጥብቀው ሊገነዘቡት ይገባል።

ይህ ሀገራችንን ወደ ከፋ አዘቅት፣ ህዝባችንንም ወደ ከፍተኛ እልቂትና ንብረት መውደም የሚገፋፋ፣ ወገኖቻችንን ሁሉ በግዴታ ተፈናቃይና ስደተኛ የሚያደርግ ሁኔታ እንዲቆም ጊዜው ሳይረፍድ ሁላችንም በአንድነት ልንነሳ ይገባል። በአሁኑ ሰዓት ምክሩም፣ ጥሪውም፣ ተግባሩም አንድና አንድ ብቻ ነው። ይህም ዘልቆ መሄድ ያለበት፤ ደምቆ መታየት ያለበት፣ ጎልቶ መሰማት ያለበት ተነሱ የሚል ድምፅ ብቻ ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ የሀገራችን ጉዳይ ያገባናል የምንል ኢትዮጵያውያን ሁሉ በአስቸኳይ መመካከርና መፍትሄ መቀየስ እጅግ አጣዳፊ ተግባራችን መሆን ይገባዋል።

ሸንጎ ይህን አደጋ በመገንዘብ ማንኛውም ድርጅት ወይም ስብሰብ የኢትዮጵያን አንድነትና የሕዝቧን ደህንነት መሠረት በማድረግ መፍትሄ ለማፈላለግ በሚጠራው የምክክር ስብሰባ ላይ ተገኝቶ የበኩሉን ድርሻ ለማበርከትና ጊዜው የሚጠይቀውን ወቅታዊና አጣዳፊ መፍትሄም ለመፈለግ ያለውን ፍላጎት ያሳውቃል።

በሀገራችን ውስጥ አሁን እየተከሰተ ላለውና ለሌሎችም እጅግ አደገኛ ሁኔታዎች ምንጩ ህወሓት መራሹ የኢህአዴግ አግላይና አምባገነን ሥርዓት መሆኑን ሁሉም ተገንዝቦ፤ በማንኛውም ቦታ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ሁሉ ከእርስ በርስ ግጭት አንዱ በሌላው ላይ ከመዝመት እንዲቆጠብና ለዘመናት ካስመዘገበው የመዋደድ፣ የመፋቀርና የሠለጠነ ባህሉን ታላቅነት በዚህ ፈታኝ ጊዜ ደጋግሞ እነዲያስመሰክር ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ጥሪያችንን እናሰተላልፋለን።

አሁን አገራችን ያለችበትን ከፍተኛ አደጋ በማስተዋል፣ ይህም አደጋ በአገር አንድነትና በህዝብ ህይወት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጥፋት በመገንዘብ የአገሪቱ መከላከያ ኃይል ከአንድ የፖለቲካ ድርጅት አገልጋይነት ራሱን በማግለል አገራዊና ታሪካዊ ሀላፊነቱን እዲወጣ እናሳስባለን። እያንዳንዱ የመከላከያና የፀጥታ ኃይል አባል፣ ታማኝነቱ በመጀመሪያ ደረጃ ለአገሩና ለሕዝቡ መሆኑን አንጠራጥርም። ታዲያ አገሩንና ወገኑን የከዳ አገዛዝ ቁራሽ እንጀራ እየጣለ ሂድና ወንድምና እህትህን ግደል ሲለው እምቢ ማለት ለኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ ከቶም ይሳነዋል ማለት አንቃጣም። ሲሆን ሲሆን ሕዝብ እንዲወጋበት የተሰጠውን መሣሪያ እናትና አባቱን ገሃነመ እሳት ውስጥ አስገብቶ በሚጠብሳቸው ሥርዓት ላይ እንዲያዞር ለመላው ሠራዊት አስቸኳይ መልዕክት እናስተላልፋለን።

በተጨማሪ የኢትዮጵያና የህዝቧ ደህንንት ከአንድ ፖለቲካ ድርጅት ጠባብ ጥቅምና ፍላጎት በላይ ናቸው። የሠራዊቱ አባላት በታሪክ አጋጣሚ የተገኘ ሀላፊነታቸውን ለታላቋ ሀገራችንና ሕዝባችን አንድንት፤ ደህንነትና እኩልነት መንከባከቢያ እንጂ ለጥፋት እንዳያውሉት አደራ እንላልን፡፡

ከዚህ በላይ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብና ለሠራዊቱ ያስተላለፍነው መልዕክት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ጎጠኛው አገዛዝ የሥርዓቱ ዋና ምርኩዝ አድርጎ ከሚጠቀምባቸው መዋቅሮች አንዱ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና መንግሥታዊ ኮርፖሬሽኖች ውስጥ የሚሠሩ ሙያተኞችንና ሠራተኞችን ነው። የሲቪል ሰርቪስ አባላት በጥቂት ሆድ-አደሮች ፍራቻ ሥርዓቱን ቢያገለግሉም አብዛኞቹ ለአገራቸውና ለህዝባቸው እንደሚቆረቆሩ ሸንጎ ያምናል። አሁን አገራችን አጠቃላይ በሆነ ቀውስ በምትናጥበት ጊዜ የሲቪል ሰርቪስ አባላት ዝምታቸውን ጠብቀው ይቆያሉ ብሎ ማመን ያዳግታል። በየካቲት አብዮት እንደሆነው ሁሉ የሲቪል ሰርቪስ አባላት ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ሲቀላቀሉ ሥርዓቱ ሊሽመደመድ እንደሚችል አያጠራጥርም። የሲቪል ሰርቪስ አባላት ማኅበሮቻቸውን በማጠናከር፤ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በብዛት በመቀላቀል፣ የሥራ ማቆም አድማ በመጥራትና ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ አገር-አድን የሆነውን ትግል እንዲቀላቀሉ ሸንጎ አበክሮ ይጠይቃል።

ሸንጎ ደግሞ ደጋግሞ እንደገለጠው ሀገራችን ውስጥ መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ መምጣት እጅግ አስፈላጊ ነው። አገራችንና ህዝባችን ለ26 አመታት በተጫኗባቸው የአንድ ድርጅት አምባገነናዊ አስተዳደር ሥር በፍጹም ሊቀጥሉ አይችሉም። አምባገነናዊው ሥርዓት ተወግዶ ህገ-መንግሥታዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እውን ለማድረግ ደግሞ በጋራ ትግል፤ በብሄራዊ መግባባት፣ በሰጥቶ መቀበል፣ አሳታፊና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ የህዝብንና የአገርን አንድነት በሚያጠናክር መልኩ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሸጋገር አሰፈላጊ እንደሆነና ለዚህም እንደሚታገል ሸንጎው ያረጋግጣል።

የሸንጎ ራዕይ የቂም በቀል አዙሪት ተበጣጥሶ እኩልነትና ፍትህ የሰፈነባት፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በኩራት የሚኖርባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ነው። የጦርነት፣ የእስራት፣ የንብረት ነጠቃና የስደት አዙሪትን በመስበር በሀገራችን ምድርም ዳግም እንዳይከሰት ማድረግ ነው። እነዚህን ራዕዮች እውን ለማድረግ ደግሞ በሰፊ የተቃዋሚ ኅብረት የሚመራ የህዝብን ትግል ማፋፋም ለነገ የማይባል መሆኑን በድጋሚ አጽንዖት ሰጥቶ መታገል አስፈላጊ ነው።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : **shengo.derbiaber@gmail.com**